**መፅሔት #021**
**ተደራሽ የታክሲ ማበረታቻ ፕሮግራም**
**ከጃንዋሪ 1, 2022 ጀምሮ ተግባራዊ የሚሆኑ የፕሮግራም ለውጦችን ዝመና**
**ዲሴምበር 15፣ 2021**

የዚህ መፅሔት አላማ በተደራሽ የታክሲ ማበረታቻ ፕሮግራም ላይ ለኢንዱስትሪው ወቅታዊ መረጃ መስጠት ነው።

**ዳራ**

- በኖቬምበር 17፣ 2021፣ በማህበረሰብ ልማት ኮሚቴ አጀንዳ ውስጥ ተደራሽ የታክሲ ማበረታቻ ፕሮግራም አጭር መግለጫ፣ CDC 2021-1559 ተካቷል።
- አጭር መግለጫው በተደራሽ የታክሲ ማበረታቻ ፕሮግራም እና በWAV Calgary የተማከለ የመላክ አገልግሎት ላይ የተደረጉ ለውጦችን መረጃ አካቷል።
- አጭር መግለጫው እና አራት ተያያዥ አባሪዎች በኦንላይን አጀንዳ (online agenda) የካልጋሪ ከተማ ድረ-ገጽ ላይ በአንቀፅ 11.1 ላይ ይገኛሉ።

**ለውጦቹ ምንድን ናቸው?**
ሙሉ የለውጦቹ ዝርዝሮች በካልጋሪ ከተማ ድህረ ገጽ ላይ በተለጠፈው የዘመነው ተደራሽ የታክሲ ማበረታቻ ፕሮግራም ማዕቀፍ ውስጥ ይገኛሉ። ለዓመታዊ ማበረታቻዎች (እስከ 5,000 ዶላር) ባለው የገንዘብ ድጋፍ መጠን ላይ ምንም ለውጥ የለም እናም በWAV Calgary የመሣሪያ ስርዓት በኩል ለተጠናቀቀ ለእያንዳንዱ ተደራሽ ጉዞ በየጉዞው አዲስ የአሽከርካሪ ማበረታቻ በመተዋወቅ ላይ ነው። በፕሮግራሙ ላይ የተደረጉ ለውጦች **ከጃንዋሪ 1፣ 2022** ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናሉ።

የሚከተለው በፕሮግራሙ በኩል የሚቀርቡ የማበረታቻዎች ማጠቃለያ ነው፡-

| የክፍያ ዓይነት | አመታዊ ማበረታቻዎች | | በየጉዞ የአሽከርካሪ ማበረታቻ (አዲስ) |
|---|---|---|---|
| **ተቀባይ** | ትክክለኛ እና ቀጣይነት ያለው የATPL ባለቤት | ትክክለኛ እና ቀጣይነት ያለው የTDL ባለቤት እንዲሁም ተደራሽ ተሽከርካሪን ለማንቀሳቀስ ድጋፍ ያለው እና hATPL ጋር ቁርኝት ያለው | ትክክለኛ እና ቀጣይነት ያለው የTDL ባለቤት እንዲሁም ተደራሽ ተሽከርካሪን ለማንቀሳቀስ ድጋፍ ያለው እና hATPL ጋር ቁርኝት ያለው (በWAV Calgary የመሣሪያ ስርዓት ላይ) |
| **መጠን (ድግግሞሽ)** | እስከ $3,000 ዶላር (በዓመት) | እስከ $2,000 ዶላር (በዓመት) | h4am እስከ 6pm መካከል ለተጠናቀቀ ለእያንዳንዱ የዊልቸር ተደራሽ ጉዞ $10 ዶላር<br><br>h6pm እስከ 4am ለተጠናቀቀ ለእያንዳንዱ የዊልቸር ተደራሽ ጉዞ $20 ዶላር |
| **የክፍያ መርሃ ግብር** | ከጁን የATPL እድሳት ቀጥሎ | ከመንጃ ፍቃድ እድሳት ቀጥሎ (በልደት ቀን) | በየሩብ ዓመቱ |
| **የብቁነት መስፈርት** | የደንበኛ አገልግሎት እና የደህንነት መስፈርቶችን ከማሳካት ጋር የተቆራኘ | የደንበኛ አገልግሎት እና የደህንነት መስፈርቶችን ከማሳካት ጋር የተቆራኘ | ጉዞዎች በWAV Calgary የመሣሪያ ስርዓት በኩል መጠናቀቅ አለባቸው |

**ሌሎች ለውጦች፦**

- ለዓመታዊ ማበረታቻዎች ብቁ ለመሆን የሚያስፈልጉ የመስፈርቶች ብዛት ቀንሷል።
- ተደራሽ የታክሲ ማበረታቻ ፕሮግራም ማዕቀፍ የፕሮግራም መስፈርቶችን አለማክበርን የበለጠ ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመፍታት እናም ፕሮግራሙ ወጥነት ባለው እና ግልጽነት ባለው መልኩ መካሄዱን ለማረጋገጥ ተሻሽሎ ተጠናክሯል።
- አዲሱን በየጉዞው የሚደረጉ የአሽከርካሪ ማበረታቻዎችን እና WAV Calgary ከሙከራ ወደ ሙሉ ፕሮግራምነት የሚያደርገውን ሽግግር ለመደገፍ፣ ከታክሲ ድለላ የጥገና ዋጋ ቅናሽ (Taxi Brokerage Maintenance Rebate) የገንዘብ ድጋፍ ወደ ተደራሽ የታክሲ ማበረታቻ ፕሮግራም እየተዘዋወረ ነው።

ይህ መጽሔት በአማርኛ፣ በአረብኛ፣ በሂንዲ፣ በፑንጃቢ፣ በሶማልኛ እና በኡርዱ ቋንቋ በCalgary.ca ላይ ይገኛል።

የተደራሽ ታክሲ ማበረታቻ ፕሮግራምን በተመለከተ ማንኛቸውም ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎ ltsengagement@calgary.caን ያነጋግሩ።

ከሰላምታ ጋር፣



አብዱል ራፊህ
ዋና የLivery መርማሪ
የካልጋሪ የማህበረሰብ ደረጃዎች